# መሠልጠን ወይንስ መሠይጠን




**መግቢያ**

በቀና ልቡና አዳዲስ ግኝቶችን ባመጡ ሳይንቲስቶች
እጅግ ተበራክተው ዘመናዊ መገልገያ መሳሪያዎች፥
የሰው ልጅ ምድራዊ (ሥጋዊ) ሕይወት ሲሻሻል፥
በአንጻሩ ሥልጣኔ ለበጎ ነገር ብቻ እንዳይውል፥
በውስጡ ክፉ ነገር በዝቶና ተራብቶ፥

በሰይጣናዊ ስርዓት ተተክቶ፥

ይኸው!... ገዳይ መርዙን ቀምሰን ታመናል፥

ምድራዊ እድገትና መሻሻል ሥልጣኔ ያልነው፥

ተቀይሮ ሥይጣኔ ሆኖብናል።

ምንድነው የሥልጣኔአችንን መልክ የሚቀይረው?

ሰይጣናዊ የሚያደርገው።

ወይንስ ምን እየጎደለው ነው?

የሰብእናችንን ደረጃ ቁልቁል እንዲያድግ የሚያደርገው?

ከጥሩው ሥልጣኔ መጥፎነት ሲወጣው፥

ክፉው ሥልጣን ይዞ - ሥልጣኔን ሲመራው፥

የሰው ልጅ የሠለጠነ መስሎት፥

ተስቦ - በሥጋዊ ድሎት፥

ሥይጣኔ ነው ሥውር ጠላት የሆነበት።

የዚህ ጽሑፍ አላማ -

በምድራችን ከጥሩው መጥፎው አይሎ እያየነው፥

የዘመኑ ሥልጣኔ ሰውን ወደ ክፋት - ወደ ሥይጣኔ ሲገፋፋው፥

ወይንም ሰው ራሱ ሥልጣኔን ለሥይጣኔ ሲያውለው፥

“ማንም ሰው ያሻውን ያድርግ..” በሚል መርሆ እንዳንተወው፥

ጥሩነታችንን ከውስጣችን እንድንመረምር፥

ከጥሩ ነገር ጎን የሚያድጉ ክፉዎችን እንድንቆጣጠር፥

በሥጋዊ ኑሮአችን መንፈሳዊነታችን እንዲከብር።

መጥፎ ጊዜ ላይ ደርሰናልና - ቆም ብለን ብናስብ፥

አዲስ ሥልጣኔም ብንፈጥር፥

ካሁን በኋላስ የትምህርቱ አይነት እንዳይሆን፥

በምድራዊነት ላይ ብቻ የሚያተኩር።

የእግዚአብሔርን ጽድቁን ብንሻ - በአዲስ ሥልጣኔም ብንመራ፥

በሥጋዊ ኑሮአችን ሳንከፋ - መንፈሳዊ አይናችን ይበራ።

**<u>መሠልጠን ወንስ መሠይጠን</u>**

ካለማወቅ ወደማወቅ መሸጋገር፥
አውቆም እውቀትን መተርጎም በተግባር፥
ለዚህም የሚያበቃውን ትምህርት መማር፥
እውቀትን ማዳበር
የዳበረውንም እውቀት በሥራ መተርጎም፥
በግብርና፥ በቴክኖሎጂ፥ በሶሻል፥
በኢኮኖሚ - በፖለቲካም
ሁሉን መሥራት - ከስንፍና ከድንቁርና መውጣት፥
በሁለ ዘርፍ ግልጋሎት - ለሰው ልጅ የሚጠቅም
አቅርቦትና ዝግጅት ማመቻቸት፥
ከምድሪቱ የሚበላና የሚጠጣ - ቆንጆ ነገር ማብዛት፥
ትልቅ መሆን - አምሮ ደምቆ መታየት፥
ጥሩ ጥሩ ነገር እየፈጠሩ ኑሮን ማመቻቸት፥
ይህ ከሆነ ሥልጣኔ ማለት፥
ይህንን ማን ጠልቶ ነው - በምንስ ምክንያት
ሥልጣኔ እንደ መጥፎ የታየበት?
ማን ጠልቶ ነው ምቾት - ምንስ ክፋት ተገኝቶበት?
ሥልጣኔ ተገቢውን ክብር የተነፈገበት፥
ጥሩ የተባለው ጥሩ ከሆነ፥
ጥሩውን የሚጠላ ማን ሆነ?

ጥሩ የተባለው ጥሩ ሆኖ ሳለ - ሰው ከጠላው፥
ጥሩውን የማይወድ ያ ሰው ችግር አለው?
ነው? ወይንስ ጥሩው ነው ችግር ያለው?
አባቶቻችን ጥሩውን ሥልጣኔ ሲያሞግሱ፥
ልጆቻቸው ሃብታም ሲሆኑ
ተምረውና ሥራ ይዘው፥
አንዳንዶችም ወዳጅ ዘመድ ሲረዱ ራሳቸውን ችለው፥

በዚህ ጥሩ ውጤት ሥልጣኔ ባመጣው፥
ደስታው ለሁላችንም ነበር፥
ከሥልጣኔ ጎን የበቀለውን ሰንኮፍ እስክናየው።
ለሰንኮፍም ምንጭ ይኖረው ዘንድ ግድ ነው፥
የሰውን ክፋት ከምድሪቱ - የምድሪቱን ክፋት ከሰው፥
የሰውን በጎ ፈቃደኛነትም ከግዴታዊነቱ የሚለየው፥
በቂማ እውነተኛ እውቀት ነው ሰው ያነሰው።
ጥሩና መጥፎ በዚች ምድር፥
ውስጡ ጭቅጭቅ ውስጡ ክርክር፥
በጎነት በበጎነቱ ያለው ሕይወት አጭር፥
ደስታም በደስታነቱ አይዘልቅ - አይሰምር፤
እስቲ ማነው ከሰአታት አልፎ ቀናትና ወር፥
ደስ እያለው ሳያዝን ሳይተክዝ የሚኖር?
ታዲያ በቂ እውቀት - እውነተኛ እውቀት
ዘለአለማዊ እውነት - ሊኖር አይችልም በዚች ምድር
ምን በጎ ነገር ቢዘንብ፥
ሥልጣኔም እንደ በጎ ነገር ቢቆጠር፥
በጎነትን ከውስጡ የሚያወጣ ሠይጣናዊ ኃይል፥
ደጉንም ነገር ከውስጡ ያወጣዋል፥
ወይንም በክፋት ይበርዘዋል።
ዘመናዊ ሥልጣኔ ከነሰንኮፉ፥
ሰውን የሚያደርግ ራስን ወዳድ - ክፉ፤
ፍቅር ሲሸረሸር - ትህትና ሲቆጠር እንደ ሞኝነት፥
ውሸት መዋሸትም እንደ ብልጠት፤
ያ ከአባቶቻችን የወረስነው መልካሙ ጠባይ -
መልካሙ ባህላችን - ጨዋነት - ደግነት፥
በክፉውም በደጉም አብሮ መሆን - መረዳዳት፥
እንደ ድንቁርና ተቆጥሮ፥

ሰውን በማንነቱ ማክበር ቀርቶ፥
በመንፈስ የከበረ ሰው ሁሉ በሥጋውና በነፍሱ ብቻ
እንደ ሌጣ ሰው ሆኖ፥
ሰማያዊ ክብሩን ተገፎ፥
ምድራዊ ክብርን ተጎናጽፎ፥
በምድራዊ ሃብት የከበረ ሲገን፥
በምድራዊ ሃብት የደኸየ ሲኮነን፤

ሕዝበ አዳም በውሸት አለም ውስጥ ሲሠለጥን
ጥሩውን ሲጥል - ሲከተል መጥፎን፥
ቀስ በቀስ ሰውም ራሱ ሲለወጥ - ሰይጣናዊ ሲሆን፥
እኛም ኢትዮጵያውያን በእኛነታችን፥
ለራሳችን ጉራማይሌ - ባይተዋር፥
ከእኛነታችን ባህርይ ፈጽሞ በራቀ - የውጪ ሥልጣኔ ስንነከር፥
ይህ ነው መሠይጠን ማለት
ለውጥና - መሻሻል - የሚሉት - ሳያስቡት መቀየር።

<u>ማነው ለሥይጣኔ ተጠያቂው</u>

ከስነ ምድር እስከ ስነ ጠፈር - እውቀት በእውቀት ላይ ሲዳብር፤
የጠፈር መንኮራኩር - ለበለጠ ምርምር፥
የሰው እውቀቱ - ሥልጣኔውም ከምድራችን አልፎ ሲሻገር፤
እጅግ ገነነ የምድራዊ ሥልጣኔ ነገር።

ታዲያ የከፋት ምንጩ ማነው - ምንድነው?
የሰውን ክፋት ከምድሪቱ - የምድሪቱን ክፋት ከሰው
ይህንን ለይያቶ ማስቀመጥ ነው ያስቸገረው።

የዘመኑን ሥልጣኔ ምንጩን - ወደኋላ ስንጎትተው
ሄኖክ በጊዜው በከፍተኛ የመመልከት ችሎታው፥
መላእክት ከፈጣሪ ፈቃድ ወጥተው - በነእስማዚያ በኩል - በአለቆቻቸው
የጦር መሳሪያ ግንባታና የመሳሰሉትን ለሰዎች በማስተማራቸው፥

ኃጢአተኞች ናቸው ሲል ከሰሳቸው። (ሄኖክ 2፡ 1-41)
ይህንን የጥንቱን እንደ ሥልጣኔ ምንጭ መቁጠር ብዙ አያስኬድም፥
የዘመኑ ሥልጣኔ አመጣጡ ከአንድ ሥፍራ/አካባቢ ቢመስልም፥
በብዙ ጊዜ የእውቀት ድርብርቦሽ እንጂ ባንዴ አልመጣም።
ግን - ወደድንም ጠላንም፥
ህብረተሰቡ ፍቅረ ሰብን በፍቅረ ገንዘብ ሲለውጠው፥
እንቅስቃሴውን ከአኢ (አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ) ከሚመራው፥
ከቁስ አካል ጋር ሲያጣምረው፤
የራሱን ተኢ (ተፈጥሮአዊ ኢንተሊጀንስ) ሲያዳፍነው፤
የዛን ጊዜ ነው የዘመኑ ሥልጣኔ ሰውን ያረከሰው፥

ገንዘብ እና አኢ እንዲህ ሰውን ከበላይ ሆኖ ሲመራው፥
በቁስ አካሎች እንቅስቃሴ ቁጥጥር ውስጥ ሲያስገባው፥
የሰው ልጅ ወደ ታች የማደጉ ሂደት ለሚታየው፥
የወደፊቱ እጅግ የከፋ - እጅግ አስጊ ነው የሚሆነው።

<u>**ምድራዊ ትምህርት (እውቀት)**</u>

የአለም ሕዝብ ወደ ሥይጣኔ የተሳበው፥
በእርግጥ ከትምህርቱ ነው?
ከጥንትም ጥሩነት - መንፈሳዊነት ከጎደለው?
ወይንስ የትምህርቱን አጠቃቀም ባለማወቅ ነው
ህብረተሰብ ራሱን ወደ ሥይጣኔ የመራው?
ለጥያቄዎቻችን ብዙ መልሶች ቢኖራቸውም፥
የማናውቀውና ሊገባን የማይችል ቢኖርም፥
የሥልጣኔአችንን መነሻና መዳረሻ መመርምር አይከፋም።
የዘመኑ ሥልጣኔ ምንጩ አንድ - አስተዳደጉም አንድ፥
የብዙ ጊዜ ምርምር ውጤት
የእውቀት ግንብ - የዳበረ በትምህርት።
መጀመሪያ አመጣጡ ከጥቂት የሰሜን ሰዎች

እውቀት ከተገለጠላቸው ፈላስፎች - ሳይንቲስቶች።

ለሰፊ የእውቀት ግንባታ፥

የሳይንስ፥ የሂሳብ፥ የታሪክ፥ ወዘተ. ትምህርቶች

መማርና ማስተማር ተጀመረ ሁሉንም በተርታ፥

እስከ ዘመኑ ሥልጣኔም ተደረሰ - ከብዙ ዓመታት ጀምሮ በዝግታ።

የቀድሞ ሥልጣኔ - የግብጽ የኢትዮጵያ፥

የህንድ የቻይና፥ የአራቢያ የፐርሺያ፥

የአዝቴክ፥ የኢንካ፥ የማያ፥

ተዳፍኖ ቀረ - ከፍ ሳይል ባለበት ተቀበረ፤

የአውሮፓው አንሰራራ - ከፍ ከፍ አለ - ተጠናከረ፤

በጥቂት ሩቅ አሳቢዎች አይምሮ የሰረገ እውቀት፥

እርስ በርሱ እየተያያዘ - እየተደጋገፈ

ለዘመኑ ሥልጣኔ መሠረት ሆነ።

ከየት መጣ ሳይባል፡-

አጠቃላይ (ሁለ ገብ) የእውቀት ጮራ ፈንጥቆ፥

በእነ አሪስቶትል (384–322 BC) - በፕላቶ (427–347 BC)

ፍልስፍና ተስፋፍቶ፥

በነአርቺመደስ (287–212 BC) እና ሌሎችም

ማተማቲክስ (ሂሳብና ስሌት) ቀን አግኝቶ፥

በአይዛክ ኒውተን (1642–1727) የካልኩለስ ግኝት

ሳይንስ ኢንጂኔሪንግ እጅጉን ዳበረ፤

እንደ ዘመናችን አይነት የህክምና ምርመራ

በሂፖክራተስ (460–370 BC) ተጀመረ፤

በጆህን ዳልቶን (1766–1844) በድሚትሪ ሜንዴሌቭ (1834–1907) እና ሌሎችም

የኬሚስትሪ ሊቃውንት፥

ይታወቅ ጀመር

የንጥረ ነገር ጠባይ - አይነትና ብዛት።

በሉይስ ፓስተር (1822–1895) ሲታወቅ የባክተሪያ (ጀርሞች) እርባታ፥

እጅግ ተሻሻለ የሃኪም ቤቶች ሥራ፤
በማሪ ኩሪ (1867–1934) የበስባሽ ንጥረ ነገሮች ግኝታ
በኤክስሬይም ግልጋሎት የካንሰር በሽታ
በመጠኑም ቢሆን ተገታ።
በኒኮላስ ኮፐርኒከስ (1473–1543)፥ በጋሊሌኦ ጋሊሊ (1564–1642)፥
ጆሃነስ ኬፐለር (1571–1630)፥ ኤድሞንድ ሃሌይ (1656–1742)፥
ኢድዊን ኸብል (1889–1953) እና ሌሎችም የከዋክብት ጥናት
በጠፈር መካከል ምድራችንን እንደ አንድ የውሃ ጠብታ አስቆጠራት።
ከአልፍሬድ ኖቤል (1833–1896) የፈንጂ (ዲናሞ) ግኝት ይልቅ፥
በአልበርት አይንስታይን (1879–1955) በንጥረ ነገር ይዘት እና ፍጥነት ጥምረት፥
በትንሽ ነገር - በኃይል በመምታት ታላቅ ጉዳት፤
በሚሳይል በሮኬት ኑክሊየር ቦምብ አወናጭፎ
ከሰማይ እሳት አዝንቦ ሕይወት ማጥፋት፤
ማቃጠል መፍጀት - ማውደም፥ ምድራዊ ገሃነም እሳት…።
በትንሽ እንጨት የሰላ ብረት ሰክቶ - ጦር ሰብቆ ከመዋጋት፥
በታንክና በመድፍ ወይንም በመትረየስ ጥይቶችን አርከፍክፎ
ሰውን ከነንብረቱን ማደባየት፥
ይህንንም እንደ ሥልጣኔ እድገት ሳንቆጥር አናልፈው፥
ከሰው የሰረጸ እውቀቱና ክፋቱ ተጋምደው ነውና ከዚህ ያደረሰው።
ግን ግርም የሚለው፡-
የሰው እውቀቱ ወደ ክፋት ቢወስደውም፥
ወደ ጥሩነት የሚገፋ እውቀትም አላጣም።
በእስቲቨን ሃውኪንግ (1942–2018) እና ሌሎችም የፊዚክ ሊቃውንት
በጽልመተ ጥልቀት የጠፈር ውስጥ ግፊት…፥
መዞር መሽከርከር በበዛበት፥
ለጠፈርም ከመዘረጋት ጋር የጠፈር መሰብሰብ እንዳለበት[1]፥

---

[1] ስለ ጠፈር መሰብሰብ - ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሦስተኛ መጽሐፍ - ገጽ 39።
https://www.amharicbooksforunity.org/amharicbooksforunity

ይህንንም ተማርን - እጅግ የረቀቀ የፊዚክ ትምህርት፥
ተመስገን፤
የሳይንስ እውቀታችን፥
የስነ ምድር - የጠፈር ምርምራችን፥
የእግዚአብሔርን ሥራ እንድናደንቅለት አደረገን....፤

*ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥*

*የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል...። መዝ. 18፥1*

ከዋክብት አገረ ከዋክብት - እኛም ተደምረን
ተመስገን የእግዚአብሔር ምስክሮች ለመሆን አበቃን።
በተጠቀሱትና በሌሎችም - በአለም ዙሪያ የነበሩና ያሉ ሳይንቲስት
ለአለማችን ስላበረከቱ ታላቅ እውቀት፥
ሲዘከሩ ይኖራሉ - በክብርና በአድናቆት።
ግን በዚህ ጽሑፍ እንደ ሳይንቲስይት የማይቆጠር
ዳርዊን የተባለ የሥይጣኔ መምህር
የእግዚአብሔርን ዝግመተ ለውጥ
በመገኘት እንጂ በመፈጠር እንዳልሆነ ሲያመሳክር፥
ሳይንስ መሳይ መርዝ እርሱ የነሰነሰው፥
ሃቀኛ ሳይንቶስችንም ነበር ያወናበደው።

*"ዳርዊን የከጀለው፥ ሰውን ከዝንጀሮ በሆሚኒድ ሊያዛምደው፥*
*ዝንጀሮን በፕሪሜትስ ከአንትሮፓይዳ ሊያገናኘው፥*
*እንዲህ እያለ ወደ አንዲት ህዋስ ሰውን ሊመልሰው።"*[2]

እንዲህ ሰውን መንፈስ አልባ የሚያደርግ እጅግ በማኮስስ፥
አሁንም በዘመናችን ልዩ ኢሳይንሳዊ ትምህርት ይሰበካል -
የቀጥተኛ ስነ አመክንዮ ቀውስ፥
ከቁስ አካላዊ አስተሳሰብ እንዳንወጣ በሚጋርድ

---

[2] ከምድራዊነታችን ባሻገር - ሦስተኛ መጽሐፍ ገጽ 128 - https://www.amharicbooksforunity.org/amharicbooksforunity

ወደ ጥሩው እንዳንጠጋ በሚታገለን በእርኩስ መንፈስ።
ታዲያ እንዲህ በሁለት ኃይላት የተወጠረ ሰው
እንዴት ነው ካለመሰይጠን ኑሮውን የሚመራው?
እስከ 16ኛው ዘመን ድረስ
ሥልጣኔ በዝግታ እያደገ ቆይቶ፥
ሳይንሳዊ አብዮት ድንገት ፈንድቶ፥
በነሚካኤል ፋራደይ፥ ጄምስ ዋት፥
በነቶማስ ኤዲሰን እና ሌሎችም፥
ጽንሰ ሃሳብና ተግባረ እድ እርስ በርስ ተጋምደው፥
ሲንቀረፈፍ የነበረውን ሥልጣኔ አጣደፈው፤
እውቀትንም ከምቾት ጋር እንዲጣመር አደረገው።
የእንፋሎት ግፊት ሞተር እና ኀማ - የኢሌክትሪክ ሙቀትና ብርሃን፥
መኪና ባቡር ሮኬት አይሮፕላን፥
ሬዲዎ ቴሌቪዢን፥
ስልክ ኮምፑተር ፔኒሲሊን............፥
እንግዲህ ማን ይጠላል ምቾትን?
ገንዘብ ያለው የሚሸምተውን፤
ከድሎትም ድሎት ሥራን የሚያቃልል ፕሮግራም በኮምፑተር፥
ለፋብሪካ፥ ለእርሻ ሥራ - ለትምህርት ለምርምር፤
ሮቦት የኮምፑተር ውጤት - ለሰው አሽከር ይሆን ጀመር።
የዘመኑ ሥልጣኔ መሠረቱ ምድራዊ እውቀት ሆነና፥
በምድራዊ እውቀት ሰው ሥጋዊ ምቾቱን ገነባና፥
በውስብስብ የእውቀት መንገድ ሲሄድ ሲሄድ
መንፈሳዊ ጠባይን በሚያርቅ - ሰማያዊ አመለካከትን በሚጋርድ፥
ማህበራዊ ጠባይን በሚያስረሳ - የሚያደርግ ራስ ወዳድ፥
ወደ ጸብ - ወደ ውሸት በሚገፋፋ - ግለኝነትን በሚያስገድድ፤
የሥልጣኔም ትሩፋቶች ሲመጡ ተደራርበው፥
የሰውን ተፈጥሮአዊ ማንነቱን ቀይረው፥

ከድሎት ጋር ኃጢአት አሠርተው።

*“የምድር ኃጥአን ሁሉ ወንጀለኞች ናቸው፤*

*ስለዚህ ምሥክርህን ወደድኩ።” መዝ. 118፡129*

ህብረተሰብ ሲሠለጥን፥

ከሥልጣኔውም ጋር ሲሠየጥን፥

“ከየት ተነስተን ከዚህ ደረስን?..” ብለን መጠየቃችን፥

ያለንበትን አቋማችንን - ሂደታችንን ከወዲሁ ተመልከተን፥

መጥፎውን ሂደት እንድንገታው፥

የተሻለ ሥልጣኔም ቢኖር እንድናስበውና እንድናገኘው፥

ይህ ቢሆን ነው ድካማችን ፍሬ የሚያፈራው።

ግን አንዳንዶች ሳይንስ እና ሳይንቲስቶችን ከሃይማኖት ያርቋቸዋል፥

ግን በእግዚአብሔር የማያምኑ ሳይንቲስቶች ከሚያምኑት ተለይተዋል፤

ለምሳሌ - ጋሊሊዎ ጋሊሊ “መጽፍ ቅዱስ ዋሾ ሊሆን አይችልም” ሲል፥

“አምላኬ አትተወኝ...” እያለም ይጸልይ ነበር ይባላል።

የታላቁ አይዛክ ኒውተን ካልኩለስ

ለውጦችን ከጊዜ ጋር አጣምሮ የማስላት ጥበብ፥

ጥልቅ በሆነ ሃይማኖታዊ ፍልስፍናው ታጅቧል[3]፤

ለብዙ ዓመታት ብዙ እውቀቶች ሲደማመሩ

የዘመኑን ሥልጣኔ በመፍጠራቸው፥

ምንም ክፋት ባይኖርም በውስጣቸው፥

መሠረተ ትምህርትን ከምድራዊነት ላይ በማንተራሳቸው፥

ለሰብአዊነት መንፈሳዊ እድገት እውቅና ባለመስጠታቸው፥

---

[3]“….The most beautiful system of the sun, planets, and comets, could only proceed from the counsel and dominion of an intelligent and powerful Being." https://en.wikipedia.org/wiki/Isaac_Newton

በዘመኑ ሥልጣኔ አንጻር - ሰማያዊ እድል ፈንታችን ጨለሙብን፥
መንፈሳዊነትን በሚሰርጽ ፍልስፍና ላይ ባለማተኮራችን
አዲስና ጻዲቅ የሆነ ሥልጣኔ አልታይ አለን።
ግን እስከዚህም ለደረስነው
ምስጋና መስጠት ያስፈልጋል - ምስጋና ለሚገባው።
በብዙ አዋቂዎች ተፈትኖ፥ ብዙ ዘመን ተሻግሮ፥
በተለያዩ የሳይንስ ትምህርቶች ጣምራነት
የአጠቃላይ የሰው ልጆች አንጎል ያፈራው፥
አማኞች - ቄሶች ከሆኑ ሃቀኛ ሳይንቲስቶችም ተውጣጥቶ
እጅግ ርቅቅ ብሎ ከዚህ የደረሰው
የእግዚአብሔር ጥበብ በሥፍራዎች ሁሉ እንዳለም ማሳያ ነው።

ነገር ግን -
ከኃጢአተኛ መላእክት - የአስተሳሰብ ተውሳክ - የማይታዩ ጀርሞች
የርዕዮት ጠባብነትን - የስነ አመክንዮ ጠማማነትን የሚያስተምሩ
ልዝብ ሰይጣኖች - እርኩሶች - ጋኔሎች - ጂኒዎች
እንደ ቀሳውስት - እንደ ሳይንቲስትም ሆነው
በሰዎች መካከል ጥልቅ የሚሉ የእርጎ ዝንቦች
ካሁን በፊት እንደነበሩ አሁንም አልጠፉም፥
ከሳይንቲስቱም፥ ከቄሱም ከሼኩም።
ትንንቅ - ትግል ቀርቶ አያውቅም፤
ግን ሰብረን ሄደናል ኬላውን -
አንዳንዴ ስንፈጥን አንዳንዴም ስናዘግም።

**<u>የዘመኑ ሥልጣኔ ሂደት</u>**

መቀላወጥ ብቻ አይበቃምና ሌሎቹን እያየን፥
የተደላደለ ምድራዊ ኑሮ እያጓጓን፤
በምድራዊ ሥልጣኔ  የቀደሙንን እየተከተልን፥
እኛም ከዘመኑ ሥልጣኔ ተካፋዮች ለመሆን በቃን።

በጥቂት አስተዋዮች አይምሮ እየተጠነሰሰ፥
ከቶ እማይደርቅ የእውቀት ምንጭ እንደ ውሃ ፈሰሰ፤
ዘመናዊውን ትምህርት ለሚማሩ ሁሉ ተዳረሰ።
የሰው ልጅ አይምሮ (ለክፉም ሆነ ለደግ) አስቀድሞ በተደነገገ፥
የእውቀት ጎዳና እየተመራ፥
በአንድ ውሱን ስነ አመክንዮ እየተገራ፥
እግዚአብሔር አስቀድሞ በፈጠረው
በተፈጥሮ ላይ ተራቀቀና፥
በንጥረ ነገሮች ውስጥ የሚሯሯጡትን ደቂቀ አካላት
ከኢሌክትሮን - ፕሮቶን እስከ ኑክሊየስ ያሉትን ሁሉ አስተዋለና፥
እውቀትን በእውቀት አሳደገ - አንዱን ባንዱ እያደራረበ፥
የሰውም ልጅም ሠለጠነ ተባለ፥
ምድራዊ እውቀትን አወቀና።

የዘመኑ ሥልጣኔ ሂደት፥
እጅግ ርቅቅ ማለትን ያገኘንበት፥
በኮምፑተር እና በሞባይል በኢሌክትሮኒክስ ፍጥነት
በሃሳብም በተግባርም ከፍ ከፍ ካደረገን - ካመጠቀን፥
ይህስ በጣም ደስ ይላል - ልጆቻችንም ጥድፍ ጥድፍ ሲሉ ማየት፤
ለሥራ ከሆነ ለመልካም ነገር፥
ለጋራ ብልጽግና - የጋራ ሃብትን ለማፍራት
ብሎም ለፍቅር ከሆነ - አብሮም ለመደሰት።

ግን ስንመልከት - በጥሩነት ጓዳ መጥፎነት
ከጥቅሙ ባሻገር አቢይ ጉዳት፥
ታዲያ ማነው ለሥይጣኔ ተጠያቂው
ሥልጣኔ ራሱ የመጥፎነትን ትምህርት የዘራው፥
ወይንስ ራሱ ተጠቃሚው
አጠቃቀሙን ያላወቀው?

የሰው ልጅ በፍጥረቱ
እንዴት ይለያል ሥጋዊነቱ - ከመንፈሳዊነቱ፤
የሥልጣኔውስ ጥሩነቱ ወይንም መጥፎነቱ፥
ተመዝኖ ሲታይ እንደ ግልጋሎቱ፥
የወደፊቱ ትውልድ ትኩረቱ፥
የሚያደላ ከሆነ ለምድራዊነቱ
ባሕሬው ተለይቶ ከሰማያዊነቱ፥
ከገዛ መንፈሱ እየራቀ ሲሄድ የሚደርስበቱ፥
ኑሮና ብልሃቱ ሰብአዊ ግንኙነቱ፥
ሲመሠረት በገንዘቡና በቁስ አካላዊ ንብረቱ፥
ሰው ከሰው፥ ሰው ከተፈጥሮ - ከእንስሳት ከእጽዋት፥
እንዲሁም ከግዑዝ መሬት
አብሮ - አምሮ - ሰምሮ መኖር ሲያቅት፥
ይህ ከሆነ የዘመኑ ሥልጣኔ ውጤት፥
ከፍቅር ወደ ጦርነት - ወደ እልቂት ማምራት፥
ምድራዊ ሕያዋንን ሁሉ አስከትሎ ጥፋት፥
ይህንን ይመስላል መጨረሻው፥
የዘመናዊ ሥልጣኔና የመሠይጠን ሂደት።

## <u>እንጻራዊ ሥልጣኔ</u>

ቀደም ሲል - የቁስ ትምህርት ስንጀምር፥
ዛሬ ተገቢውን ሥፍራ ባጣ ፊደል ስንቆጥር፥
ሁሁ - አቡጊዳ ብለን - ወደ መልእክተ ዮሐንስ ስንሻገር፥
ተፈጥሮአዊ ማንነታችን (ጠባያችን) እንዳይቀይር፥
ከሥጋዊነታችን ጎን መንፈሳዊነታችንንም እንድናጠናክር ነበር።
በምድራዊ ሥልጣኔ እጅግ ባንገፋም - ራሳችንን በራሳችን ችለን፥
ሕይወታችንን በአብሮነት - ሃዘን ደስታችንን በጋርዮሽ አድርገን፥
ኑሮን በመጠኑ ወስነን - ከመንፈሳዊነት አይላቀቅም ነበር አስተሳሰባችን፤

ከቁሰካላዊነት የረቀቀ ነበር መመልከታችን - ርዕዮተ አለማችን፤
ስለዚህ፡- ደስታን ያገኘ ነበር መንፈሳችን፥
ሳይጎዳ ሥጋችን፤
በምድራዊው አለም ሰማያዊም ይመስል ነበር ኑሮአችን።

ግን የኋላ ኋላ እኛም እንዲሁ በምድራዊው ሥልጣኔ ተማርከን፥
የተመቻቸ አለማዊ ኑሮ አጓጉቶን፥
በምድራዊነት ብቻ የተቀየሰ የኑሮ ዘይቤ፥
ወደርሱ የሚያመራውም ትምህርትና እውቀት - አለም ያደነቀው፥
ሥጋችንን ማረከው።
የእኛ የሆነውን በእጃችን የያዝነውን ጣልነው፤
ለኛ የሚሻለንን ለኛ በማይሻለን ለወጥነው፤
በማህበራዊ ኑሮ እርስ በርስ መተሳሰብ፥
በመንፈሳዊነትም መቀራረብ ቀርቶ
ግለኝነት የኑሮ ዘዴአችን ሲሆን፥
በክፋት - በኃጢአት ብዛት ታውረን፥
በሥልጣኔ ስም ሥይጣኔ ሲነግሥብን አላወቅን።
“እንካችሁ ጥበብ - ከኛ ተማሩ እውቀትን...” ሲሉን፥
“የትኛውን እውቀት - የቱን እንቀበል የቱን ትተን...?
የትኛው ነው እውቀት የትኛው ነው ጥበብ?” ሳንል፥
ተስገብግበን - ሁሉን አግበሰበስን
ሳንመርጥ ሳናማርጥ -
የሰጡንን ሁሉን ተቀብለን፤
ለውጪ ሥልጣኔ ስንል
የኛን የሥልጣኔ በር በራሳችን ላይ ዘጋን።
ትምህርታቸውን ሁሉንም ጠንቅቀን ተማርን፥
በሥልጣኔ ስም የእኛነታችንን ባህሬ በሌላ ቀየርን - ሠየጠንን።
በሥይጠኔ ስንሄድ ስንሄድ፡- “ሞኝ ውሃ ሲወስደው ይስቃል” እንዲሉ፥
በሥይጣኔ ጎርፍ እየተወዛወዝን፥

“የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች” እንዲሉ፥
የተመኘነውን የፈለግነውን ስላገኘን እየተደሰትን፥
“ሰማይ ይናዳል ብሎ ባላ ተከለ” እንዲሉ፥
የውጪውን የሥልጣኔ ምሰሶ ባገራችን ተክለን፥
የኛን የራሳችንን መንፈሳዊ ሥልጣኔ ጥለን፥
ከነርሱው ተምረን - ተምረን
የኛ ባልሆነው አለም ውስጥ ስንኖር፥
ሳናስበው እነርሱኑ መሰልን፤
የጣልነውን እኛነታችንን አጎንብሶ መመልከት አሳፈረን።
በዛ በቆሰ ትምህርት ውስጥ - ንቀን በተውነው
በድቁና የሚከፈት
ልዩ ጥበብ ነበር ሲከፈት የሚታየው፥
ለምንበላው ለምንጠጣው ምሥጋና ቢኖረው፥
ኑሮአችን - እንቅስቃሴአችን ትርጉም ነበረው።
“ለዘብልአነ ዘንተ ሕብስቱ
ወለዘአስተየነ ዘንተ ጽውዓ”
ብለን የምንበላው - የምንጠጣው
በጸሎተ ማዕድ የምናሳርገው፥
የጤንነት እና የሕይወት ትርጉም ነበረው።
ማንም ህብረተሰብ በራሱ የሚደርስበትን ሥልጣኔ
በራሱ ሥፍራና ጊዜ ማሳደግ ሳያቅተው፥
ከላይ ከሰሜን በመጣው ነው የራሱን ሥልጣኔ የለወጠው፥
የቀድሞ ሥልጣኔአችን ሲዳፈን - ሲተካ የኛ ባልሆነው፥
ያኔ ነው የተቀየርነው ቡራቡሬ መልክ የያዝነው።
ሁላችንም - ልጆቻችንን - የልጅ ልጆቻችንንም እየተከተልን
ምድራዊ ኑሮን ብቻ የሚያሻሽል - አዲስ እውቀት አይሎብን፥
በመንፈሳዊ ሥልጣኔ ማደጋችንን ትተን
ሳናውቀው በሥይጣኔ ተጠለፍን።

**<u>የዘመኑ ሥልጣኔ እና የባህሪአችን መለወጥ</u>**

ኑሮ (ደስታም ሃዘንም) የግል በሆነበት፥
ከእውነት ይልቅ ውሸት በነገሠበት፥
የተዛባ ስነ አመክንዮ - የአስተሳሰብ ጎዶሎነት፥
የቀጨጨ እምነት - የሞራል ልፍስፍስነት፥
የጥላቻ ጀግንነት - የፍቅር ድህነት፥
የአብሮነት ፍርኃት፥
የብቸኝነት ናፍቆት፤
ፈሰሰ የሰው ሃሞት፥
እጅግ ላላ የሰው እምነት፥
በግንጥል ጌጥ ማጌጥ መሽቀርቀር ብቻ ሆነ
በምድራዊ ውበት
የሰውን ምኑንም በማይገልጽ፥
በቁስ አካል ቁንጅና መርካት፥
የሰውን ተፈጥሮአዊ ማንነቱን በማይመጥን
ከመሠልጠን የተገኘ ቅሪት
እጅግ ሲበዛ ሃብት፥
ለማይገኝ ደስታ ድካም ካለ እረፍት
ወሰን ድንበር በሌለው ምኞት፥
በፍላጎትም ላይ ሲደረብ ፍላጎት
ቢበላ አይጠገብ - እንዳው መስገብገብ ለድሎት፥
ወደ ገንዘብ ጥግት፥
በመንፈስ ወደኋላ ጉትትት።
ወዴት ነው የዚህ ሥልጣኔ አጠቃላይ ሂደቱና አቅጣጫው?
ወደ እግዚአብሔር ነው የሚመራው?
ወይንስ ወደ ሰይጣን ነው የሚያስጠጋው?
ምንድነው አላማው - የትነው መዳረሻው?
ደግሞስ ማነው ለሥይጣኔ ተጠያቂው?

ሥልጣኔ ራሱ ወይንስ ተጠቃሚው?
ምንድነው - ይህ የዘመኑ ሥልጣኔ ውስጠ ባህርይ፥
የተደበቀው - ውስጣዊው?
የሰዎች ልዕልና ቢሆን የሥልጣኔ መለኪያው፥
ከየትኛው አገር ነው ከፍታው የሚታየው?
በአሜሪካ ነው? እጅግ ሥልጡን አገር በሚባለው፥
ግን በእስረኞች ብዛት ከአለም አንደኛ በሆነው?
አይ! እንዲሁም አገር ሳንጠቅስ፥
ሥልጣኔ የሚለካ ቢሆን በከተሞች እድገት - በፎቆች ትልቅነት፥
በመሃንዲሳዊ ግንባታዎች ጥራት፥
በቤቶች ትልቅነት - በክፍሎቹ ብዛት እና በእቃው አይነት፥
የተጠቃሚዎቹም የተንደላቀቀ ኑሮ ቢሆን የሥልጣኔ መለኪያው፥
ከእንዲህ ያለ ሥፍራ እኮ ነው፥
ሰው ራሱን ከራሱ ያራቀው - ሰውና ሰው የማይተዋወቀው።
በሥልጣኔ ነው በሥይጣኔ ሰው ራሱን ከራሱ የገነጠለው፥
ማህበራዊነቱን ትቶ ብቸኛ የሆነው?

> የሰው ልጅ  ምድራዊ - ሰማያዊ ሲሆን በተፈጥሮው፥
> ውስጣዊ መንፈሳዊ ተፈጥሮውን የሚቀሰቅስበት ኃይል አነሰው፥
> መንፈሳዊ ሥልጣኔ ከምድራዊነቱ አጣብቂኝ የምያላቅቀው፥
> "አልእሉ አልባቢከሙ.." እንደሚባለው፥
> ወደ ላይ ከፊ ከፍ የሚያደርገው
> ወደ ሰማያዊነቱም የሚያስጠጋው - እምነት አነሰው - ሃይማኖት ጎደለው።
> ምድራቱም በሰማያዊ ልምላሜ ደስታን የምትሰርጽ እንዳትሆን፥
> ከውስጧ መንፈሳዊነትን የሚያመነጭ ኃይል አነሳት፥
> ነፍሳማነቷን የሚሰልብ ሥልጣኔ ሳይንሳዊ መስሎ መጣባት፥
> ውስጣዊ ተፈጥሮዋን - ልምላሜዋን - እሷነቱን፥
> ከእንስሳት፥ ከእጽዋት፥ ከሰውም ጋር፥
> በአንድነት ተከባብሮ የአብሮ መኖር ጸጋዋን፥

ክብሯን ማዕረጓን ሊገፋት፥
በስግብግብነት እየቦጠቦጠ ሊያጠፋት፥
ሥልጣኔ መጣባት -
በሕያውነቷ እንዳልታወቀች - ግዑዝ ሊያደርጋት።
ታዲያ፡- ማነው ለሥይጣኔ ተጠያቂው
ሥልጣኔ ራሱ መጥፎነትን የዘራው፥
ወይንስ ራሱ ተጠቃሚው
አጠቃቀሙን ያላወቀው?
ልጆቻችን ልዩ መልክ - ልዩ ጠባይ ሲያወጡ፥
ያባቶቻቸውን የአኗኗር ዘይቤ በባዕዳኑ ሲለውጡ፥
እኛም እንዳባቶቻችን ስናስተውል - ልዩ ጠባይ ከቤታችን፥
የመንፈስ መታወክ፥
ኑሮ ብኽርታ - እንቅልፍ - ቅዠት - ሰመመን፥
እውነትና ውሸትን መለየት እስኪያቅተን፥
አዪ! አለመታደል፥
ሥልጣኔ ተብዬው ሥይጣኔ -
እውቀት ተብዬውም ድንቁርና ሲሆን፥
ምን ጊዜ መጣብን - ምን ይሆን እጣ ክፍላችን
ከዚች ባለ ሁለት መልክ ምድራችን፤
የዘመኑ ሥልጣኔ የዘመኑ በሽታ ሲሆን ምርታችን፥
አስደንብሮ ገደል ሲከተን፥
ምንም ማድረግ እስኪያቅተን።

<u>***መደምደሚያ***</u>

ሳይንሳዊ እውቀት - የሥልጣኔአችን አንቀሳቃሽ ሞተር
ብትንትን አድርጎ ሲያስተምረን የተፈጥሮን ምሥጢር፥
የኛም እምነት ጸንቶ በሳይንቲስቶች ምርምር፥
ያልተረዳነው አንድ ነገር፥

ሳንጠራጠር መግባታችን እነርሱው በከፈቱት በር፥

ሳንጠራጠር መጓዛችን እነርሱው በቀደዱት ፈር፥

የምድራችንም ሥልጣኔ - እድገቷም እነርሱው በቀየሱት መስመር፥

ለየት ባለ መንገድ - ለብቻ (በነፃነት) ማሰብ መመራመር ሲቀር፥

በመንፈስ አልባ ስነ አመክንዮ - ዘርፈ ብዙ ትምህርት፥

ምንም ክፍተት በማይሰጥ - ለሃይማኖት - ለእምነት፥

ይህ ነው ዛሬ እኛ የደረስንበት፥

በመንፈስ አልባ ሥልጣኔ ወደ ሥይጣኔ የገባንበት፥

ምድራዊ ጠቢባን - ሰማያዊ መሃይማን የሆንበት።

በእግዚአብሔር እስትንፋስ ነፍስ ዘርተን፥

ለሰይጣን እንዳይሆን ሕይወታችን

አቅጣጫን መቀየስ ያስፈልጋል እንደገና፥

ፈጽሞ አያዋጣምና የያዝነው ጎዳና።

ሰው በሰው ሲደራረብ ምድሪቱ አልበቃ ስትል፥

በእኔ ልብስ - እኔ ልኑር - ያሁኑ ራስ ወዳድነት ሲቀጥል፥

ከታች ያለው ሲጨናነቅ - እላይ ያለው ሲቀማጠል፥

ምድራችንን ለጥቂቶች የሚያውል

ሰይጣናዊ ሥልጣኔ ያከትማል፥

ምድራችንን ለሁሉም በሚያደርግ አዲስ ሥልጣኔ[4] ይተካል፤

አይቀርም፤ ይህ ይሆናል።

---

[4] ከዚህ የሚከተለውን - ወደ ቅዱስ ሥልጣኔ የሚለውን ይመልከቱ።
https://ee2463e1-1d4c-42ce-868c-8ee589c5a3cb.filesusr.com/ugd/a268ea_7a9b52a9f6994761a3d84481583521f8.pdf